# ይድረስ ከቃሊቲ በሰላም ለተለቀቁት የቅንጅት መሪወች

ክቡራን እና ክቡራት ለቆማችሁለት አላማ በማለት ሀያ ወራት በእስር ስትማቅቁ ቆይታችሁ አሁን ከምትወዱታ ከሚወዳችሁ ህዝብ በስፊዋ የመከራ እስር ቤት በሆነችው ኢትዮጵያ ከሚኖረው ወገአችሁ በመደባለቃችሁ እንኩአን ደስ ያላችሁ ከእናንተ ደስታ በላይ ህዝቡ የተደሰተ መሆኑን የምትስቱት አይደለም በተለየም ባገርቤት ያለው ለሁልጊዜ ምኞቱ እንደሌሎች ህዝቦች በነፃነት ለመኖር የሚመኘውና ለዚያም አግዝሀለሁ ተከተለኝ ላሉት ሁሉ ክቡር መስዋእትነት ሲከፍል ለኖረው። ምኞቱ ደግሞ ደጋግሞ ቀቢፅ ተስፋ እየሆነ ለተቸገረው የናንተን መፈታት ሲሰማ በጣሙ እንደተደሰተ ያያችሁት በመሆኑ ነጋሪ አያስፈልጋችሁም በዚህ ደስታ እኔም አንዱ በመሆኔ ይችን አጭር ደብዳቤ ጻፊሁ።

ይህን ካልሁ ብሁአላ ልዩ መልእክቴ ለዶክተር ብርሐኑ ይድረስልኝ።

ውድ ዶክተ ብርሐኑ እንደሚታወቀው በመጽሐፍወም እንደገለጹት እርስዎ ትግሉን ለጊዜው አቓርጠውት ( ) ቢቆዩም ለአካለመጠን ከደረሱ ጊዜ ጀምሮ በትግሉ ጎራ እንደቆዩ ይታወቃል። ያ ትግሉን የጀመሩበት ዘመን ያው ለዴሞክራሲ ተብሎ እስዎም ጓደኞችወም ዴሞክራሲ ያለገደብ ጊዚያዊ ህዝባዊ መንግስት አሁኑኑ በማለት እንደነበር አምነውም የተሰለፉበት ድርጅት ግልጽ በሆነ አታጋይ መፈክርና ፕሮግራም እናንተን የመሰለ ወርቅ የትውልዱን አባላት አሰልፎ ያታገለበት ነበር። እንደሚያውቁት በዚያ ትግል ያለፍን የትውልዱ አባላት ከመሪ እስከተራ አባላት ከጀርባ የውጭ የወዳጅም ሆነ የጠላት ተጽእኖ ሳይኖርባቸው በንጹህ ተነሳስተው መስዋእትነት ከፍለዋል። በነገራችን ላይ በጻፉት መጽሐፍ ያነን የትግል ታሪክ አጉልተው ማሳየት በተገባ ግና መቸስ ቢሆን እስር ላይ ስለነበሩ አልሆነም።

ያ ትውልድና ታጋይ መሪወቹ እንደሚያውቁት ከላይ እንደጠቀስሁት የጀርባ አጀንዳ ያልነበራቸው በመሆኑ በእምነት ታግለው ብዙወች ያለማወላወል ለጠላት እጅ ሳይሰጡ ፍጹም ነው እምነቴ ለትግሉ ነው ህይወቴ ብለው አልፈዋል። መቸም ቢሆን የሚረሳ ገድል ስላይደለ እሰዎም የነሱ መንፈስ በልቦናዎ የሚኖር ይመስለኛል ምንም ቢሆን ያ ለማደራጀት ከላይ ታች ሲል በመኟኟዣ የረዱት ዶክተር ተስፋየ ደበሳይ የመስዋእትነት ታሪክ ለሰዎ ቀርቶ አሁን ለተወለዱ አዲስ ትውልዳችን መታወቅ የሚገባው ገድል ነው።

ወደጀግኖች አምባም ወዳሲምባ ከሄዱ በሕዋላ ያገኙአቸው ኃዶችዎ ቤሳቤስቲ ሳይኖራቸው ወይም የውጭ ወዳጅ እንዲረዳቸው ያገር ደህንነትን ለሶስተኛ ሀይል አሳልፈው ሳይሰጡ በራስ የመተማመን ጽኑ መንፈስነ ይዘው  መስዋእት በመክፈል በሰበሰቡት መሳሪያ የታጋዩ ተስፋና ጀርባ የሆነውን ሰራዊት አደራጅተው ደርግ የግፍ በትሩን ሲያጠናክር ኢንደስወ በህይዎት ላሉና በትግል ላለፉ መጠለያ ሆነዋል። ትግል እንደውሀ ለጠማው የትውልዱ ታጋዮችም ተስፋ ሰጭ አብሪዎች ሲሆኑ። ላንዳንዱም የደርግ የውር ጭፍን የመደዳ ግድያ ላስበረገገው ነፍስ አትርፈዋል።

ይህን ሁሉ የምዳክረው በጻፉት መጽሐፍ ትንሽም ስንኝ ብትሆን ቦታ ሰጠው ትልቁን የጀግንነት ዘመን ትውስታወን ጠቅሰውት በማለፍወ እኔም ከሀያ ዘጠኝ አመታ በፊት ያለፉብትን የጀግንነት ገድልና በቦታው የነበሩትን በተመለከተ ነውይህን ደብዳቤ ልጽፍለወት ያነሳሳኝ።

እስወ ከሌሎች የቅንጅት መሪዎች ጋር ወደ ቃሊቲ ከሄዱ በህዋላ መቸም የእስራትን ነገር አይተዋል በማየትዎም ባካባቢ በእስር የሚንገላቱ ንጹህ ዜጎች ያሉብትን በመጽሐፍወ ገልጸውታል; እግዜር ይባርክ እጅወን ከቁርጥማት ያድነው።

እኛም በያለንበት መሪወቻችን ከእስር ይፈቱ በማለት ያልቆምንበት የፈረንጅ ግቢ አልነበረም እና። እንዴው ለመጥቀስ ያህል በ ኖቬምበር 2005 በአሜሪካን ታንክስ ጊቪንግ ይሉታል (ብሄራዊ ባእል) አቶ ቡሽ ወደ ዋናው ቻሚ መኖሪያቸው ክራውፎርድ ቴክሳስ( ) መንደር ናት ይሄዳሉ ስለተባልን ተጠራርተን አቤት ለማለት ተዘጋጀን ታዲአያ ቅንጅት መንፈስ ነው ይሉን የነበሩት የስዎ ድርጅት አባሎችን አማክረን ቀኑ ሲደርስ ይመስለኛል አቶ ያማማቶ( ) ከተባሉት የፕሬዜዳንቱ ያፍሪካ ጉዳይ አማካሪ በደረሰ ማስጠንቀቂያ መንፈሶች የበላይ አካል ትዛዝ ደርሶአቸው የማይሄዱ መሆኑን አስታወቁን

በእርግጥ ነው ያ ማስጠንቀቂያ ለሁሉም የተላለፈ ሳይሆን አይቀርም ግና መቸም ትግል በሌሎች ይሁንታ አይሆንም እና ምንም እንኩአን ግማሽ ወገኖቻችን ቢቀሩ አግር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከሁሉም አካባቢ ተጠራርተን ሄደን ነበር እግዚአብሔ ይመስገን የተሳካም ሆነልን ብዙ አለማቀፍ የዜአ አውታሮችም አዳምጡን ዋይታችንንመ ዘግበውታል። ከዚያ በፊትም በሁአላም ብዙ ሰልፍ ተደርጉአል ትቂቶቹ ግን ባስቸጋሪ ቦታና ጊዜ የተደረጉ ስለነበሩ ነው ይህንን የጠቀስሁለወት።

መቸም የማያውቁትን መንገሬ አይደለም ዋናው ግን ያኔ አብረወት የቆሙት የዚያ ትውልድ ታጋዮች ጊዜንና ድርጅትን ሳይለዩ አሁንም በየሄዱበት የጀመሩትን ላፍታም ባለማቋረጥ ደፋ ቀና ማለታቸው አልቀረም ለማለት ነው። ህዝብ የመረጣቸው ይፈቱ መሪወች ይፈቱ መዳረሻቸው ያላወቁት አንጋፋ ታጋዮች ጸጋየ ገ/መድህን(ደብተራው) ይስሐቅ ደብረጽዮን፤ በለጠ አምሀ፤ ተስፋየ፣ አበራሽ፣ ወንዱ ይፈቱ በማለት አሁንም ያለ አላቋረጠ ጥያቄ እያሰሙ ነው። በያደባባዩ ቆመዋል እንደሚያውቁት የአውርፓንና የሰሜን አሜሪካን ቅዝቃዜ ሙቀት ሳይሉ፣ ተሰልፈዋል።

የርሀብ አድማ ያረጉ እራሳቸውን አስረው ለቀናት ባስተዳድር አደባባዮች የሰነበቱ ሁሉ ነበሩበት። ይህንም ከኔበላይ ያውቁታል።

በዚህ ባሜሪካን ኮንግረስ ባውሮፓ ፓርላማ በሌሎችም አገሮችና አለማቀፍ ተቋማት የአገራችን ጉዳይ እንዲታይ ሰፊ ትግል ታይቱአል ባንዳንዶች መልካም ውጤት የታየባቸው ናቸው።
ይህም የናንተን መፈታትስ ቢሆን ከዚሁ የትግል ጫና መች እርቆ ብለዉ ነው።

እስዎ ጻፉ በተባለው መጽሐፍ ይቅርታ ተባለ ማለቱ ወህኒ ስለነበሩና በተለየም ያሳሪወችን ባህሪ የሚያውቅ እንዲየው አልዋጥ እያለ ስላስቸገረ ነው። የሆነው ሆኖ በዚያው በጻፉት ልበለው መጽሐፍ የኦነግ አባላት ደጋፊወች ብሎም የተጠረጠሩ ንጹሀን የደረሰባቸውን ሰቆቃ አላግባብ እንግልትና እስር ድንቅ አርገው አስቀምጠውታል። ከተፈቱም በህዋላ በመገናኛዎችና በስብሰባወች ደጋግመው አውስተውታል። ለየት ያለው የተጨመረ ቢኖር በምእራብ ሶማሌ ነፃ አውጭወች የሚደርሰውን በደል ማንሳትወ የሚመሰገን ነው።

ይህን ካልሁ በህዋላ እንዴው ለጥያቄ ያክል ምነው ያነን በቀጭን ቀን አገዘኝ ያሉትን የጸጋየን መዳረሻ ባያውቁም ሰምተዋል ታዲያ ለምን ይሆን በዝምታ ማለፍወ?። እግዜር ተጨምሮ የህዝብ ድምጽ ተከብሮ ቢሆን እኮ እኛም ከሰዎ ቢሮ በራፍ መሰለፋችን አይቀርም ነበር። እረስተውት ነው እንዳንል ይህን ያህል ያገር ፖለቲካ ከልጅነት እስከእውቀት የኖሩበት ነው።

ሌላው መቸም ቢሆን ኢትዮጵያውያን የናንተን መፈታት በጉጉት ጠብቀውት ነበር ምክንያቱም ያለውን የዘረኛ መንግስት ላንዴ ለመጨረሻ በናንተ አምላካዊ ታምር ታሶግዱታላችሁ በሚል ተስፋ ነበር ያሁኑ አዝማሚያችሁ ግን ትንሽ ግራ እያጋባ መጥቱአል። ወደ ጉዳየ ልመለስና መቸም አሁንም ያነኑ ቃሊቲ ተቀምጠው በላምባዲና የጻፉትን በመመርኮዝ ነው፣ ሕብረቱ የመጀመሪያ ስብሰባውን ሲጠራ ከሌላ ወዳጅዎ ጋር ወደአሜሪካ መጥተው ሁለት ድርጅቶችን ከህብረቱ እንዳይቀጥሉ ስብሰባ ጠርተዋቸው ነበር። ያም ተሳክቶላችሁ ሁለቱ ድርጅቶች ከሕብረቱ ያልረባባ ምክንያት በማቅረብ ወጥተዋል። እስወና ወዳጅወ በፍጠት የመሰረታችሁት ቀስተዳመና ያው መንፈስ ነው የተባለውን የህብረት ግንባር አቀናጅታችሁዋል። ሳይውል ሳያድር ያለቅድመ ሁኔታ ወደምርጫ የምተገቡ ሆኖ ሲገኝ ወያኔ ከሕብርቱ ጋር የጀመረውን ንግግር አቓረጠ ያም የሁአላ ሁአላ ተቃዋሚውን እጅ ከወርች አስሮ ወያኔን ወደ ዙፋኑ እናንተን ወደቃሊቲ ህዝቡን ቅስሙ ሰብሮ ብዙም ህይወት ከፍሎበት በዜሮ ተለያዬ። ይኸው ለቀባሪው አረዱት ነው የማጫውተወት።

ከሕብረቱ ላለመቀላቀል ዋና ምክንያታችሁ(ከወዳጅወ ጋር) ማለቴ ነው፡ በህብረቱ ውስጥ የተካተቱት በኢትይጵያ አንድነት ያመኑ ግን የዘር ድርጅቶች በመኖራቸው ነው ብለውናል። አሁን ያስገረመኝ ግን ቀደም ባለው ጊዜ ባልንጀሮችወ እፍ ያለ ፍቅር ከኦሮሞ ነፃውጭ ግንባርና ከኦጋዴንና ከሲዳሞ ግንባሮች ጋር ግንባር ቢጤ ፈጥረው ነበር መቸም ከእርሰዎ ፈቃድ ውጭ ነው ለማለት ያስቸግራል ሆኖም አቓምወን የሚያዉቅ በተለየም ህብረቱ ሲመሰረት ተጠናክሮ እንዳይወጣ ያሳዩትን ድካም ላስተዋለ ሁሉ ሊመስል አልቻለም ነበር ግን ከቃሊቲ ከወጡ በህዋላም ሆነ እዚያው ሆነው በጻፉት መጽሐፍ በየስብሰባው ባደረጉት ዲስኩር የጠነከረ ለነዚህ ድርጅቶች የመቆርቆር ስሜት ታይቱአል። ይህ ቢሆን ባልከፊ ግና ብዙ ወዳጆችወን ግራ ያጋባ ነገር እየሆነ ነው ለምን ቢሉ ሕብረቱ እንዳይጠናከር የደከሙበት ጉዳይ ለምን ተብሎ በዘር የተደራጁት ባገራችን አንድነትም ቢያምኑ ተደባለቁ በማለት ስለሆነ ማለቴ ነው ይህ ደግሞ ሹክሹታ አይደለም በየሄዱበት ላዳማጪ ፈቃድ ብታደርጉ ብዙ ጥያቄ ወደእስወ የሚያተኩር ነው ። ድንቅ ነው ቢሰሙት።

በኔ በኩል አልያዝ ያለኝ አነጋገር የፋራ “ፖለቲካ“ ሰጦ መቀበል “የሰለጠነ ፖለቲካ“ የሚሉት ናቸው። ምን ማለት ነው? በሌላ አይወስዱብኝ እኔን እንደገባኝ ከሆነ ወያኔ ኦነግ እና ሌኦች ጠባብ ሀይሎች የነፍጠኛ ፖለቲካ ይሉናል ታዲያ ከነዚህ ጋር እፍ ያለ ፍቅር ተይዞ የፋራ ሲሉን ያው ባዲሱ የእርሰወ አነጋገር የነፍጠኛ ማለት ነው። ይህ ካልሆነ ማስረዳቱ ተገቢ ነው እላለሁ። ሌላው “መቻቻል ይቻላል“ የምትል መፈክር ቢጤ ከቃሊቲ በወጡ ማግስት ባንድ የፓልቶክ ክፍል ተናግረው ነበር እየቆየ ሲሄድ ደጋፊወችቻችሁ በመፈክርነት ይዘዋታል። ከላይ ለትውስታ እንደጠቀስሁት ድሮ ትግሉ በዚያ ትውልድ (አንበሳ ትውልድ) ሲጀመር መፈክራችን ዴሞክራሲ ያለእድብ ቀጥሎም ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም የሚሉ ነበሩ ለዚያ እውን ለማድረግ ብዙ ተሰውተዋል። ይቅርታ ዛሬ መቻቻል ይቻላል የምለው መፈክር እንደምናየው ከወያኔ፣ ከኦነግ፣ ከሲዳሞ ነፃውጭ ግንባር፣ ከኦጋዴን ነፃ አውጭ መለት ለመሆኑ ልንጠራጠር አንችልም ይህን የምለው እየታየ ያለው የርስ በርስ ግጭት ብሎም ዎያኔን አጥብቀው የሚታገሉትን ላገር አንድነት የቆሙ ድርጅቶችን በናንተ ጎራ ያሉት ሁሉ ለማግል ሲሞክሩ ስናይ ይዛችሁት የመጣችሁት የልዩነት ባህሪይ ትቂት የማይባል ህዝብን ሐሳብ ላይ ጥሎአል።

ውድ ዶክተር ብርሐኑ ሰላምታየን በዚሁ በገቡበት የመቻቻል የሰለጠነ ብለውታል ፖለቲካ ልጨርስ። እባካችሁ የልቅ ተጃጅሎ ሌላውን የሚያጃጅል የተነቃበት የጅል ስራ ተውና መጀመሪያ ባንድ የተነሳችሁ ስምምነት ፍጠሩ ሲሆን ደግሞ ከአገር አንድነት ፈላጊ ተቃዋሚወች የትብብር ሰንሰለት ጀምሩ። ይሕ ሳይሆን ቢቀር እና በጀመሩት ከቀጠሉ ምናለ ይሉኛል የልደቱ እድል የማይዘለወት እንደሚሆን እፈራለሁ።

አክባሪዎ
የእንባ